የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፵፬
አዲስ አበባ ነሀሴ ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

27th Year No.44
ADDIS ABABA 19th August, 2021

**<u>ማውጫ</u>**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፪/፪ሺ፲፫

የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ……………………………………ገጽ ፲፫ሺ፮፻፮

**<u>Content</u>**

Proclamation No. 1262/2021

The Secretariat of the House of Federation Establishment Proclamation………...Page 13606

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፪/፪ሺ፲፫**

**<u>የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ</u>**

የፌዴሬሽን ምክር ቤት የፌደራሉ መንግሥት አባል ክልሎች፣ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መርጠው በሚልኳቸው አባላት የተመሠረተ በመሆኑ፤

ምክር ቤቱ በሕገ መንግሥቱ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር በአግባቡ እንዲያከናውን እንዲሁም አፈ ጉባዔው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፷፮ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የምክር ቤቱን የአስተዳደር ሥራዎች አቀናጅቶ ለመምራት እንዲችል የምክር ቤቱን ጽሕፈት ቤት እንደገና ማቋቋም በማስፈለጉ፤

**PROCLAMATION NO. 1262/2021**

**<u>A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE SECRETARIAT OF THE HOUSE OF FEDERATION</u>**

**WHEREAS,** the House of Federation is composed of elected representatives of Nations, Nationalities and Peoples of member states of the Federal government;

**WHEREAS,** it has become necessary to re-establish the Secretariat of the House of Federation so as to make the House properly carryout the powers and functions vested to it by the Constitution; as well as to enable the Speaker to lead administrative activities of the House vested to him under Article 66 Sub-Article (2) of the Constitution in an integrated manner;

የሚቋቋመው ጽሕፈት ቤት ምክር ቤቱን በብቃት እንዲያገለግል አድርጐ ማቋቋምና ኃላፊነቱን በብቃት እንዲወጣ የሚያስችል የራሱ አደረጃጀት፣ አሠራርና በቂ የሰው ኃይል ሊኖረው የሚገባ መሆኑን በማመን፣

በጽሕፈት ቤቱ አደረጃጀትና አሠራር ላይ ያሉ ክፍተቶችን በመሙላት ምክር ቤቱ ከደረሰበት ተቋማዊ የእድገት ደረጃ ጋር በሚመጥን መልኩ ተልዕኮውን እንዲያከናውን ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፪/፪ሺ፲፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ **"ምክር ቤት"** ማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፫ መሠረት የተቋቋመው የፌዴሬሽን ምክር ቤት ነው፤

፪/ **"አፈጉባዔ"** እና **"ምክትል አፈጉባዔ"** ማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፷፪ ንዑስ አንቀጽ (፲፩) መሠረት በፌዴሬሽን ምክር ቤት የሚመረጡ አፈጉባዔና ምክትል አፈጉባዔ ናቸው፤

**WHEREAS,** it has become necessary to re-establish the Secretariat in such a way to give efficient and effective services to the House and having proper organizational structure and sufficient manpower;

**WHEREAS,** it has become necessary to fill the gaps in the organization structure and operation of the Secretariat so that the House can carry out its mandates effectively;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby Proclaimed as follows.

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short title

This Proclamation may be cited as "The Secretariat of the House of Federation Establishment Proclamation No.1262/2021."

### 2. Definition

Unless the context otherwise requires:

1/ **"House"** means the House of Federation established in accordance with Article 53 of the Constitution;

2/ **"Speaker"** and **"Deputy Speaker"** means the Speaker and Deputy Speaker of the House elected in accordance with Article 62 Sub-Article (11) of the Constitution;

፫/ **"አጣሪ ጉባዔ"** ማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፹፪ መሠረት የተቋቋመ የፌደራል የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ማለት ነው፤

፬/ **"ኮሚቴዎች"** ማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፷፪ ንዑስ አንቀጽ (፲) መሠረት በምክር ቤቱ የሚቋቋሙ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ናቸው፤

፭/ **"አስተባባሪ ኮሚቴ"** ማለት አፈጉባዔው፣ ምክትል አፈጉባዔ፣ የቋሚ ኮሚቴዎች ሰብሳቢዎች፣ በምክር ቤቱ በቋሚነት የሚሰሩ የቋሚ ኮሚቴ ጸሐፊዎች፣ እና ያለድምጽ ቃለ ጉባዔ በመያዝ የጽ/ቤቱ ኃላፊ የሚሳተፉበት በምክር ቤቱ የተቋቋመ ኮሚቴ ነው፤

፮/ **"ጽሕፈት ቤት"** ማለት የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ማለት ነው፡፡

**፫. የጾታ አገላለጽ**

በዚህ አዋጅ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

## ክፍል ሁለት
## የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት

**፬. መቋቋም**

፩/ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ከዚህ በኋላ "ጽሕፈት ቤቱ" ተብሎ የሚጠራ ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል በዚህ አዋጅ እንደገና ተሻሽሎ ተቋቁሟል፡፡

፪/ የጽሕፈት ቤቱ ተጠሪነት ለአፈጉባዔው ይሆናል፡፡

3/ **"Council of Constitutional Inquiry"** means the Council of Constitutional Inquiry of the Federal Government established in accordance with Article 82 of the Constitution;

4/ **"Committees"** means the standing and ad hoc committees to be established by the House as per Article 62 Sub-Article (10) of the Constitution;

5/ **"Coordinating Committee"** means a committee established by the House comprising the Speaker, the Deputy Speaker, Chairpersons of the Standing Committees, Secretaries of the Standing Committees who work for the House permanently as well as the Head of the Secretariat who participates in the committee without any voting right;

6/ **"Secretariat"** means the Secretariat of the House of Federation.

**3. Gender Expression**

In this Proclamation any expression in the masculine gender includes the feminine gender.

## PART TWO
## THE SECRETARIAT OF THE HOUSE OF FEDERATION

**4. Establishment**

1/ The Secretariat of the House of Federation hereinafter referred to as "the Secretariat" is hereby re-established by this Proclamation as an organ having legal personality.

2/ The Secretariat shall be accountable to the Speaker.

## ፭. የጽሕፈት ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

ጽሕፈት ቤቱ አፈጉባዔው በሚሰጠው አመራር መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-

፩/ ለምክር ቤቱና ምክር ቤቱ ለሚያቋቁማቸው ኮሚቴዎች፣ ለአፈጉባዔ እና ለምክትል አፈጉባዔ አጠቃላይ አስተዳደራዊ፣ ሙያዊ፣ የጽሕፈት፣ የመስተንግዶና የመረጃ አገልግሎት ይሰጣል፣

፪/ በአፈጉባዔው ወይም በምክትል አፈጉባዔው ውሳኔ መሠረት በወቅቱ ለአባላት የስብሰባ ጥሪ ያስተላልፋል፣ አጀንዳዎችንና ተፈላጊ ሰነዶችንም ያሰራጫል፤

፫/ ምክር ቤቱ፣ አፈጉባዔው፣ ምክትል አፈጉባዔው እና እንግዶች አስፈላጊውን የመስተንግዶ አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል፤

፬/ የምክር ቤቱና የጽሕፈት ቤቱ፡-

ሀ) ቃለ-ጉባዔዎች፣ ውሳኔዎች፣ ሰነዶችና መዛግብቶች፤ እና

ለ) አስፈላጊ የሆኑ መጽሐፍት፣ ጥራዞች፣ ጥናታዊ ጽሑፎችና መረጃዎች፤

በአግባቡ ተሰብስበው፣ ተመዝግበውና ተደራጅተው አገልግሎት እንዲሰጡና እንዲጠበቁ ያደርጋል፡፡

፭/ የምክር ቤቱን ውሳኔዎች፣ ተልዕኮና አሠራር የሚመለከቱ ጉዳዮችን የያዙ መጽሔቶች፣ ጋዜጦችና በራሪ ጽሑፎች አዘጋጅቶ እንዲታተሙና እንዲሰራጩ ያደርጋል፤

## 5. Powers and Functions of the Secretariat

As per the directive given by the Speaker, the Secretariat shall have the powers and functions to:

1/ Render general administrative, professional, clerical, reception and information services to the House and its committees, Speaker and Deputy Speaker;

2/ Based on the decisions of the Speaker or Deputy Speaker of the House, call members for the meeting as well as distribute agenda and necessary documents;

3/ Deliver reception services to the House, Speaker, Deputy Speaker of the House and guests;

4/ Arrange that:

a) minutes, decisions, documents and books of accounts; and

b) necessary books, handouts, research papers, as well as other documents of the House and the Secretariat;

are properly collected and organized to render appropriate service.

5/ Prepare, publish and distribute magazines, journals, and pamphlets concerning the decisions, work procedure and mission of the House;

፮/ በምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር፣ አሠራር አደረጃጀትና አግባብነት ባላቸው ሕጎች ዙሪያ ጥናትና ምርምር እንዲያደርግ የሥራ መመሪያ ሲሰጠው ወይም በእራሱ ተነሳሽነት ጥናት ያካሂዳል፡፡ ውጤቱንም ከሙያዊ አስተያየት ጋር ያቀርባል፤

፯/ የክልሎችና የፌደራል መንግሥት የጋራ ተብለው የተመደቡና የተሰበሰቡ ገቢዎች በሁለቱ መካከል የሚከፋፈሉበትን እንዲሁም የፌደራሉ መንግሥት ለክልሎች ድጎማ የሚሰጥበትን በየጊዜው እየተሻሻለ የሚሄድ ቀመር የሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት አዘጋጅቶ ለኮሚቴው ያቀርባል፤

፰/ ምክር ቤቱ የፌደራሉ የልማት አውታሮች ሥርጭት ለኢንቨስትመንት ትርጉም ያላቸውና ፍትሐዊ መሆናቸውን ክትትል ለማድረግ የሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት ጥናት በማካሄድ ሙያዊ አስተያየት ያቀርባል፤

፱/ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ባቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ከምክር ቤቱ ሙያዊ አስተያየት እንዲቀርብ ሲጠየቅ ወይም ትርጉም አያስፈልግም በማለት በሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ሲቀርብ ጥናት አድርጎ ሙያዊ አስተያየት ያቀርባል፤

፲/ ሕዝቡ ስለምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባራት እንዲያውቅ በተለያዩ መንገዶችና ዘዴዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ይሰራል፤

6/ Undertake study and research pertaining to the powers, functions, working procedures, organizational structure as well as relevant laws when directed or on its own initiation and submit the result with professional recommendation;

7/ Prepare progressive formula for the division of revenues derived from joint Federal and State tax sources and the subsidies that the Federal government may provide to the States based on the direction given from the concerned Standing Committee of the House and submit the same to the Committee;

8/ To ensure equitable distribution of Federal infrastructure and its importance to investment activities, the Secretariat, based on the direction to be given by the concerned Standing Committee, conduct study and submit professional recommendation to the Committee;

9/ Undertake study and provide recommendation when the House requires for such recommendation on the recommendation of the Council of Constitutional Inquiry or when the appellant lodged an appeal against the decision of the Council of Constitutional Inquiry;

10/ Devise various ways with a view to aware the public on the powers and functions of the House;

፲፩/ አንድ የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ለመፍጠር የሚያግዙና ሕግ ሊወጣላቸው የሚገቡ የፍትሐብሔር ጉዳዮችን የሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት ያጠናል፣ ይለያል፣ ለኮሚቴው ያቀርባል፤

፲፪/ የሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ማንነቴ አልታወቀልኝም፣ የራስ በራስ ማስተዳደር መብቴ ተሸራርፏል፤ ቋንቋዬን፣ ባህሌን እና ታሪኬን የማሳድግበት ሁኔታ አልተመቻቸልኝም፣ በፌደራል አስተዳደሮች ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብቴ አልተከበረም የሚል አቤቱታ ሲቀርብ ጥናት ያካሂዳል፡፡ የጥናቱንም ውጤት ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ ያቀርባል፤

፲፫/ በክልሎች መካከል፣ በክልልና በፌደራል መንግስት እንዲሁም ሌሎች አለመግባባቶች እንዲጠኑ ሲታዘዝ የዳሰሳ፣ የትንተና እና የመከላከያ ስትራቴጂ በማጥናት የጥናቱን ውጤት ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ ያቀርባል፤

፲፬/ የምክር ቤቱ የአገር ውስጥና የውጪ ግንኙነት የተሳካና የተቃና እንዲሆን ይሠራል፤

፲፭/ በብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የመብት ጥያቄ መነሻነት ለምክር ቤቱ የቀረቡ አቤቱታዎች ሲመሩለት በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት መርምሮና አጣርቶ እንደ አስፈላጊነቱም ጥናት በማድረግ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ ሙያዊ አስተያየት ያቀርባል፤

11/ As per the direction of the concerned Standing Committee, it studies, identifies and submits civil matters which require the enactment of laws to establish and sustain one economic community;

12/ Undertake study, as per the directive given by the concerned standing committee and submit the outcome of the study to the concerned Standing Committee, when any community who believes that its self-identities are denied, its rights of self-administration is infringed, promotion of its culture, language and history are not respected submit an application to the House.

13/ Undertake assessment, analysis, develop strategy as well as study and submit the outcome to the concerned Standing Committee where ordered to examine disputes between States, States and Federal government as well as other misunderstandings;

14/ Work so as to make the domestic and international relations of the House successful;

15/ Upon the direction given by the House, investigate, examine and as may be necessary study complaints raised by Nations, Nationalities and Peoples' pertaining to their rights and submit professional recommendation to the concerned Standing Committee;

፲፮/ ምክር ቤቱ ያሳለፋቸው ውሳኔዎች፣ ትዕዛዞች፣ መመሪያዎችና አቅጣጫዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ለመከታተል የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ አፈጻጸማቸውንና ያስገኙትን ውጤት ክትትልና ግምገማ በማድረግ ሙያዊ አስተያየት ያቀርባል፤

፲፯/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

፲፰/ የምክር ቤቱን ዓመታዊ በጀት ያዘጋጃል፤

፲፱/ በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር ዙሪያ ስላከናወናቸው ተግባራት ዓመታዊ የዕቅድ አፈጻጸም እና ፋይናንስ ሪፖርት ለአፈጉባዔው ያቀርባል፤

፳/ በምክር ቤቱና በአፈጉባዔው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## ፮. <u>የጽሕፈት ቤቱ አደረጃጀት</u>

፩/ ጽሕፈት ቤቱ የምክር ቤት አባል ያልሆነ ባለሙያ በአፈጉባዔው አቅራቢነት በምክር ቤቱ አስተባባሪ ኮሚቴ የሚሾሙ የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ እና ምክትል ኃላፊ ይኖሩታል፡፡ ተጠሪነታቸውም ለአፈጉባዔው ነው፡፡

፪/ እንደ አስፈላጊነቱ የሚወሰን ዳይሬክተሮች እና ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

፫/ ዳይሬክተሮች በአፈጉባዔው ይሾማሉ፤ ተጠሪነታቸውም ለጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ይሆናል፡፡

፬/ በንዑስ አንቀጽ (፫) የተጠቀሰው እንዳለ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ ዳይሬክተሮች ባላቸው የትምህርት ዝግጅት መሠረት የሚመደቡ ይሆናል፡፡

16/ Establish working procedure to Follow up the implementation of the decisions, orders, directives and directions passed by the House; by follow up and evaluate their enforcement and outcome shall submit professional recommendation;

17/ Own property, enter into contract, sue, and be sued in its own name;

18/ Prepare annual budget of the House;

19/ Prepare performance and financial reports of the Secretariat and submit the same to the Speaker;

20/ Perform such other duties assigned to it by the House and the Speaker.

## 6. <u>Organization of the Secretariat</u>

1/ The Secretariat shall have Head and Deputy Head who are professionals and non-member of the House to be recommended by the Speaker and appointed by the Coordinating Committee; the Head and Deputy Head of the Secretariat are accountable to the Speaker.

2/ The Secretariat shall have Directors and the necessary staff whose number is to be fixed as may be necessary.

3/ Directors shall be appointed by the Speaker; they are accountable to the Head of the Secretariat.

4/ Subject to Sub-Article (3) of this Article, Directors may be appointed by taking into account their educational background.

፯. **የጽሕፈት ቤቱ የሠራተኞች አስተዳደር መመሪያ፣ አደረጃጀትና የደመወዝ ስኬል**

፩/ የጽሕፈት ቤቱ የሠራተኞች አስተዳደር መመሪያ በአስተባባሪ ኮሚቴው ሲጸድቅ ሥራ ላይ ይውላል፡፡

፪/ የጽሕፈት ቤቱ አደረጃጀትና የደመወዝ ስኬል የመንግሥትን የኢኮኖሚ አቅም ባገናዘበ መልኩ የፌደራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ መሠረታዊ መርሆዎችን ታሣቢ በማድረግ ተዘጋጅቶ በምክር ቤቱ አስተባባሪ ኮሚቴ ይጸድቃል፡፡ ሲጸድቅም በሥራ ላይ ይውላል፡፡

፰. **የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ሥልጣን እና ተግባር**

፩/ የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ የተመለከቱትን የጽሕፈት ቤቱን ሥልጣንና ተግባራት ያስፈጽማል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ፡-

ሀ) በአፈጉባዔው በሚሰጠው አመራርና የጽሕፈት ቤቱን የአስተዳደር ደንብ በመከተል የጽሕፈት ቤቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፤

ለ) በጽሕፈት ቤቱ የአስተዳደር መመሪያ መሠረት የጽሕፈት ቤቱን ሠራተኞች ያስተዳድራል፤

7. **Employees Administrative Directive, Organizational Structure and Salary Scale**

1/ The Secretariat's Employees Administrative Directive shall be implemented upon approval by the Coordinating Committee.

2/ The Secretariat's organizational structure and salary scale shall be prepared in a manner that takes into account the economic capacity of the Country and shall be implemented up on approval by the Coordinating Committee.

8. **Powers and Duties of the Head of the Secretariat**

1/ The Head of the Secretariat shall exercise the powers and functions of the Secretariat specified in Article 5 of this Proclamation.

2/ Subject to Sub-Article (1) of this Article, the Head of the Secretariat shall:

a) direct and administer the Secretariat in accordance with the direction to be given by the Speaker and in accordance with the Adminstrative Regulation of the Secretariat;

b) administer the employees of the Secretariat in accordance with Administrative Directive of the Secretariat;

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ የተመለከተውን የጽሕፈት ቤቱን አደረጃጀት መዋቅርና የደመወዝ ስኬል ለአስተባባሪ ኮሚቴ ያቀርባል፤ በአስተባባሪ ኮሚቴው ሲጸድቅ በሥራ ላይ ያውላል፣

መ) ከአፈ-ጉባዔ በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት የጽሕፈት ቤቱን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ አዘጋጅቶ ለአፈ-ጉባዔው አቅርቦ ያጸድቃል፣

ሠ) ምክር ቤቱ በሚሰጠው አቅጣጫና ስለ በጀት አጸዳደቅ በሚወጣው ደንብ መሠረት የምክር ቤቱን በጀት ያዘጋጃል፤ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሲወሰንም ሥራ ላይ ያውላል፤

ረ) ለጽሕፈት ቤቱ በተፈቀደለት በጀትና ባዘጋጀው የሥራ እቅድ መሠረት የፋይናንስ ሕግን ተከትሎ ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣

ሰ) የጽሕፈት ቤቱን የሥራ እቅድና የፋይናንስ አፈጻጸም ሪፖርት ወቅቱን በመጠበቅ አዘጋጅቶ ለአፈ-ጉባዔው ያቀርባል፣

ሸ) ጽሕፈት ቤቱ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ጽሕፈት ቤቱን ይወክላል፣

ቀ) የምክር ቤቱን ዓላማና ተልዕኮ ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

c) submit the Secretariat's organizational structure and salary scale as provided in Article 7 of this Proclamation to the Coordinating Committee; and implement the same upon approval;

d) as per the directive to be given by the Speaker, prepare the annual work plan of the Secretariat and submit to the Speaker for approval;

e) as per the directive to be given by the House and in accordance with the Regulation to be issued regarding budget approval, prepare annual budget of the House; implement the same upon approval by the House of Peoples' Representatives;

f) effect expenditure in conformity with financial laws as well as in accordance with the approved budget and action plan of the Secretariat;

g) prepare performance and financial reports of the Secretariat and submit the same to the Speaker;

h) represent the Secretariat in its relations with third parties;

i) perform such other functions so as to fulfill the objective and mission of the House.

**፱. የጽሕፈት ቤቱ ምክትል ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር**

፩/ በጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

፪/ የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶት ይሰራል፡፡

**፲. በጀት**

ጽሕፈት ቤቱ ለምክር ቤቱ የተመደበውን ዓመታዊ በጀት በፋይናንስ ሕግ መሠረት ያስተዳድራል፣ በአግባቡም ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

**፲፩. የሂሣብ መዛግብት**

፩/ ጽሕፈት ቤቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሂሣብ መዛግብት ይኖሩታል፡፡

፪/ የጽሕፈት ቤቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፣ ሆኖም አፈጉባዔው በማናቸውም አስፈላጊ ጊዜና ሰዓት የሂሣብ መዛግብት ሰነዶች በከፊልም ሆነ በሙሉ በዋናው ኦዲተር ወይም በዋና ኦዲተር በሚሰየም ኦዲተር እንዲመረመር ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ክፍል ሦስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፲፪. ደንብ የማውጣት ሥልጣን**

ምክር ቤቱ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነትና ተግባራት ለማከናወን ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ደንብ ለማውጣት ይችላል፡፡

**9. Powers and Duties of the Deputy Head of the Secretariat**

1/ Perform responsibilities directed to him by the Head of the Secretariat.

2/ Act on behalf of the Head of the Secretariat in his absence.

**10. Budget**

The Secretariat shall administer the annual budget allocated to the House in accordance with financial law and make sure that the budget is utilized appropriately.

**11. Books of Accounts**

1/ The Secretariat shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ Books of accounts and financial documents of the Secretariat shall be audited by the Auditor General annually; Provided, however, that the Speaker may order books of accounts and documents be audited, wholly or partly at anytime he deems it necessary by the Auditor General or by the Auditor assigned by the Auditor General.

## PART THREE
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**12. Power to Issue Regulation**

The House may issue Regulation when it founds necessary to exercise the powers and functions given by this Proclamation.

## ፲፫. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

፩/ አስተባባሪ ኮሚቴው ይህን አዋጅ ወይም ምክር ቤቱ የሚያወጣውን ደንብ ለማስፈጸም የተለያዩ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ የጽሕፈት ቤቱ ሠራተኞች የሚተዳደሩበትን መመሪያም አስተባባሪ ኮሚቴው ያወጣል::

## ፲፬. <u>የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>

፩/ ይህን አዋጅ የሚቃረኑ ማናቸውም ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና የአሠራር ልምዶች በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

፪/ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፶፮/፪ሺ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

## ፲፭. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከጸደቀበት ከሰኔ ፴ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም**

**ሳሕለወርቅ ዘውዴ**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 13. <u>Power to Issue Directives</u>

1/ The Coordinating Committee may issue Directives for the implementation of this Proclamation and Regulations to be issued by the House.

2/ The Coordinating Committee shall issue Employees Administrative Directive of the Secretariat.

## 14. <u>Repealed and Non-Applicable Laws</u>

1/ Laws, Regulations, Directives or Customary practices that are inconsistent with this Proclamation shall be of no effect with matters provided for under this Proclamation.

2/ Proclamation No. 556/2008 of the Establishment of the Secretariat of the House of Federation is hereby repealed by this Proclamation.

## 15. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force up on the date of its approval by the House of Peoples' Representative on the 7th day of July, 2021.

**Done at Addis Ababa, on this 19th Day of August, 2021.**

**SAHLEWORK ZEWDE**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**